ዴሞ ቀጽ 13

ይህ የፋሽስቶች ጥርቅም ያጠለቀው ኢ.ህ.ዲ.ሪ የኢትዮጵያን ህዝብ እምብ
ዛም አላደናገረም፣ አላታለለውም:: ህዝቡ የፋሽስታዊ መንግሥት ቁጥጥር በጠነከ
ረባቸው አካባቢያች አድርግ የተባለውን አሁንም ቢሆን ሳይወድ በግድ ያደርጋል::
ይህንን አስገድዶ መሰብሰብ፣ አስገድዶ ማዘመት፣ --- አስገድዶ "በውሳኔ-ህዝብ"
ማሳተፍ፣ አስገድዶ "ማስመረጥ"ና "መመረጥ" ---- የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ
ነው ካለ "ዴሞክራሲው"እና "ኢህዲሪው"በውሀ-ይለቅለት! ፋሽስታዊው ደርግ ሥል
ጣን ከያዘበት ዕለት አንስቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠርነት፣ፍጅትና ዕልቂት፣ ድህነት፣
ድርቀት፣ ችግር፣ ስደት፣ ስቃየት፣ እመቃ፣ ጭቆና፣ ምዝበራ፣ ካልሆነ በቀር ደስ
የሚያሰኘው ርስ በርስ "የምሥራች" የሚባባልበት፣ የሠላም፣ የእፎይታ፣ የመሻሻል፣
የልማት፣ የነፃነትና የመብት ጮራ የሚያይበት ጊዜና ሁኔታ አሰገጠመውም:: ትና
ንት እነዚያን ታጋጊ ወጣቶች ያለርህራሄ ጨፍጭፎ ጥይት የበሳሳውን አስከሬናቸውን
ለወላጆችና ለዘመዶቻቸው ዘላለማዊ ማስቅጠጪያ ይሆን ዘንድ በየደጃፋቸው ዘርሮ
ያሳየና ለገደለበት ጥይትም ገንዘብ ያስከፈለ ደርግ ዛሬ ስለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ
መብቶች ቢዘላብድ ማን ያዳምጠዋል? ደብ እንኳን "ቁርበት አንጥፉልኝ" የሚል ከማ
ይታወቀበት አገር ደርሶ ነው:: ለ13 የመከራ ዓመቶች ያህል አብዮታውያንን፣ ዴሞ
ክራቶችንና አገር ወዳዶችን፣የብሔር ጭቆናን የሚቃወሙ ታጋዮችን፣ ---- እያሳደደ
ሲገድሉ የኖሩት እየገደሉም ያሉት በኢሠፓና በደርግ ውስጥ የተሰገሰጉት አውሬዎች
ዛሬ ኢህዲሪ የሚባል ለምዱ ለብሰዋልና ወደ ገራም የቤት እንስሳነት ተለውጠዋል
ነው የሚሉን? እኛስ ካልቀበርናቸው አናምንም!

-ሕዝቡ በፋሽስቶች "ሕገ-መንግሥት"፣ "ኢህዲሪ"-- አይወናበድም!

-ሀገራችን የአምባገነኖች፣የአብሪተኞች መፈንጪያ አትሆንም!

-በተራዘመው ሕዝባዊ ትግል ሕዝቡ ዱላ እንደሚቀዳጅ
አንጠራጠርም!

-እ ና ቸ ን ፋ ለ ን ! ! !